# በዩኬ ውስጥ የመስራት ቱል ኪት

## በዩኬ ውስጥ የመስራት መብት

የእንግሊዝ ዜጋ ካልሆኑ በስተቀር፣ ዩኬ ውስጥ የመስራት መብት እንዳልዎት ማረጋገጥ የሚጠበቅብዎ ሲሆን ቀጣሪዎች አንድን ሰው በህገወጥ መንገድ ቀጥረው ቢገኙ የገንዘብ ቅጣት ሊቀጡ ወይም በእስር ሊቀጡ ይችላሉ።

ዩኬ ውስጥ ከ 20 በላይ አይነት ልዩ የስራ ፍቃዶች ያሉ ሲሆን ዝርዝሩ በመደበኛነት ማሻሻያ ይደረግበታል። ዩኬ ውስጥ ለመስራት የሚያስችልዎ ትክክለኛው ቪዛ ያልዎት መሆኑን ለማወቅ ይህን የኦንላይን አገልግሎት ይጠቀሙ።

### ተጨማሪ ጥልቅ መረጃ ለማግኘት ስዕሎቹ ላይ ወይም ማስፈንጠሪያዎቹን ይጫኑ

| | |
|---|---|
| **የመስራት መብትን ማረጋገጥ**<br> | የስደተኝነት ደረጃዎን በኦንላይን ማየት እንደሚችሉ ከተነገርዎ በዩኬ ውስጥ የመስራት መብትዎን ለማረጋገጥ የማጋሪያ ኮድ ማግኘት ይችላሉ። ኮዱ የሚያገለግለው ለ 30 ቀናት ሆኖ ለቀጣሪዎች ሊጋራ የሚችል ሲሆን እነርሱም የሚከተሉትን ሊያረጋግጡ ይችላሉ:<br>• ለመስራት የተፈቀደልዎትን የስራ አይነት<br>• ዩኬ ውስጥ ለምን ያክል ጊዜ ርዝመት መስራት እንደሚችሉ<br>• ጥቅማ ጥቅሞች መጠየቅ የሚችሉ ወይም የ NHS አገልግሎቶችን የሚያገኙ ስለመሆኑ<br>• የባንክ ሂሳብ መክፈት ስለመቻልዎ<br>የማጋሪያ ኮድዎን በ መንግስት ድረገጽ በኩል ማግኘት ይችላሉ። ፓስፖርትዎ ወይም የመታወቂያ ካርድዎ፣ የባዮሜትሪክ/አሻራ የመኖሪያ ፍቃድ(BRP) ወይም ቪዛ እና የባዮሜትሪክ የነዋሪነት ካርድ ቁጥር ያስፈልግዎታል። |
| **ብሔራዊ የመድን ዋስትና ቁጥር ምንድን ነው?**<br> | NINO የብሔራዊ መድን ዋስትና ቁጥርን የሚወክል ሲሆን ግብር እና ለብሔራዊ መድን ዋስትና ለመክፈል እና ጥቅማ ጥቅሞችን ለመጠየቅ በማጣቀሻነት ያገለግላል።<br>ለእንግሊዝ ዜጎች ዕድሜያቸው 16 ዓመት ሲሞላቸው NINO ይሰጣቸዋል። ለስደተኞችም NINO ይሰጣቸዋል። ሆኖም፣ ይህ ለእያንዳንዱ የመስራት መብት ላለው ሰው የማይሰራ በመሆኑ ለአንዱ ማመልከት ሊኖርብዎ ይችላል።<br>ያለ NINO ስራ ሊጀምሩ ይችላሉ ነገር ግን ብሔራዊ የመድን ዋስትና መዋጮዎችዎ እና የሚከፍሉት የግብር ክፍያ በትክክል በስምዎ መመዝገባቸውን ለማረጋገጥ አንዱ ሊኖርዎት ይገባል። ይህ እስከ 16 ሳምንታት ሊወስድ ስለሚችል በተቻለ ፍጥነት ይህን ማድረግ ጠቃሚ ነው። |
| **የሰራተኛ እጥረት ዝርዝር**<br> | የሰራተኛ እጥረት ዝርዝር የዩኬ የንግድ ድርጅቶችና ቀጣሪዎችን የሰራተኞች እጥረት ያሉባቸው ስራዎችን የሚያሳይ ዝርዝር ነው።<br>ጥገኝነት የሚጠይቁ ሰዎች መስራት የማይፈቀድላቸው ቢሆንም ጥያቄያቸው ያለ ምንም የእነርሱ ስህተት ከ 12 ወራት በላይ መልስ የማያገኝ ከሆነና ብቁ ሆነው ከተገኙ በሰራተኛ እጥረት ዝርዝር ላይ ለተገለጹ ስራዎች ለማመልከት ብቁ ይሆናሉ።<br>እነዚህን ስራዎች የመስራት መብት ለማግኘት ለዩኬ ቪዛዎች እና ኢሚግሬሽን ማመልከት ይጠበቅብዎታል። |
| **የማሳወቅና የማገድ አገልግሎት** | በዩኬ ውስጥ ያሉ ብዙ ስራዎች የወንጀል መዝገብ የኋላ ታሪክ ማጣራትን ይጠይቃሉ። እነዚህ በአብዛኛው ከህጻናት፣ አረጋውያን እና አካል ጉዳተኛ ሰዎች ጋር መስራትን ይይዛሉ።<br>የማሳወቅና የማገድ አገልግሎት (DBS) ቀጣሪዎችዎ የወንጀል መዝገብዎን የሚያጣሩበት ዘዴ ነው። ማጣሪያዎቹ የሚደረጉት በዩኬ ውስጥ ብቻ ነው። ባለፉት 5 ዓመታት ውስጥ ዩኬ ውስጥ ካልኖሩ ከትውልድ አገርዎ 'የመልካም ሥነ ምግባር የምስክር ወረቀት' እንዲሰጥዎ ማመልከት ሊኖርብዎ ይችላል። የማመልከቻ ሂደቱ ከአገር አገር ይለያያል።<br>እነዚህን መዝገቦች ከአገርዎ ማግኘት ሊከብድዎት ስለሚችል ቀጣሪዎችዎን እንደ ተጨማሪ የባህሪ የድጋፍ ደብዳቤዎች የመሳሰሉ አማራጭ ማጣሪያዎችን እንዲጠቀሙ ማነጋገርዎ ጠቃሚ ሊሆን ይችላል። |



በተጨማሪም በህግ ሙያተኛ ፊት የተሰጠ ‘ቃለ መኃላ’ ማቅረብ ይችላሉ።

አንዳንድ የወንጀል ፍርዶች ‘ያበቁ’ ተደርገው ስለሚወሰዱ መገለጽ አያስፈልጋቸውም። ሆኖም፣ ሕጎቹ ውስብስብ ስለሆኑ የወንጀል ፍርድ ካለብዎ ስለዚህ በቀጣሪዎ የሚጠየቁ ስለመሆኑ በተመለከተ ምክር ቢጠይቁ የተሻለ ነው።

## ዋና ዋና ነጥቦች

1. **ያለ ትክክለኛ ሰነድ ዩኬ ውስጥ መስራት ህገወጥ ነው**
2. **ቀጣሪዎች ለመስራት ብቁ መሆንዎን ለማረጋገጥ የማጋሪያ ኮድ መጠየቅ አለባቸው**
3. **ለመስራት ወይም ጥቅማ ጥቅሞችን ለመጠየቅ ለብሔራዊ የመድን ዋስትና ቁጥር ማመልከት አለብዎ**
4. **በዩኬ ውስጥ ያሉ ብዙ ስራዎች DBS ተብሎ የሚጠራውን የወንጀል መዝገብ የኋላ ታሪክ ማጣራትን ይጠይቃሉ።**

## ጠቃሚ ማስፈንጠሪያዎችና የመረጃ ምንጮች

- Citizen’s Advice እንደ ስደተኝነት ደረጃዎ ላይ ተመስርቶ ማቅረብ ስለሚኖርብዎ የተለያዩ ሰነዶች የተመለከቱ ብዙ ግልጽና በቀላሉ ለመረዳት የሚቻሉ መረጃዎችና ምክር አለው።
- የአሁን የዩኬ የስራ ቪዛዎች ወቅታዊ ዝርዝር
- ብሔራዊ የመድን ዋስትና መዋጮዎች ምንድን ናቸው?
- Migration Justice ፕሮጀክት ጥገኝነትን የሚጠይቁ ሰዎችን ጥያቄያቸው መልስ እየተጠባበቀ ባለበት ወቅት ለስራ ፍቃድ እንዴት እንደሚያመለክቱና ማመልከት የሚችሉ ስለመሆን አለመሆኑ እንዲገነዘቡ የሚረዳቸውን መመሪያ አዘጋጅቷል።
- ከA-Z (ሀ-ፐ) አገራት እና ለውጭ አገር የወንጀል መዝገብ ማጣሪያዎች የማመልከቻ ሒደት
- በደህንነት/ጥበቃ አገልግሎቶች ላይ ለመስራት ለሚያስፈልገው ለSIA ፍቃድ ለሚያመለክቱ ሰዎች ቃለ መሀላን እና የሥነ ምግባር ድጋፍ ደብዳቤን የተመለከተ የመንግስት መመሪያ።
- የወንጀል መዝገብ ካለዎ Unlockትመረጃ፣ ምክርና ድጋፍ ሊያቀርብልዎ ይችላል።

# በዩኬ ውስጥ የመስራት ቱል ኪት

## የሥራ ቅጥር አይነቶች

የሥራ ቅጥሮች በአብዛኛው ከሚከተሉት ሶስት ምድቦች መካከል በአንደኛው ስር ይካተታሉ፡

**የግል ዘርፍ** – እነዚህ ለባለቤቶቻቸው ትርፍ የሚያመጡ ኩባንያዎችና የንግድ ድርጅቶች ናቸው። ድርጅቶቹ የገንዘብ ድጋፍ የሚያገኙት ከዕቃዎችና አገልግሎቶች ሽያጭ ነው። የእነዚህ ምሳሌዎች ሱቆች፣ ሆቴሎች፣ መጋዘኖችና ፋብሪካዎችን ያጠቃልላሉ።

**የመንግስት ዘርፍ** –እነዚህ በመንግስት የሚተዳደሩ ድርጅቶች ናቸው። ድርጅቶቹ አገልግሎቶችን ማህበረሰቡን ተጠቃሚ ለማድረግ የሚያቀርቡ ሲሆን ክፍያቸውን በግብር መልኩ ያገኛሉ። እነዚህ ትምህርት ቤቶችን፣ ሆስፒታሎችን እና የአካባቢ ካውንስሎችን ያጠቃልላሉ።

**የበጎ ፍቃደኝነት ዘርፍ** – ይህ በተጨማሪም 'ሶስተኛ ዘርፍ' ተብሎ የሚታወቅ ሲሆን የበጎ አድራጎት ድርጅቶችን፣ የማህበረሰብ ቡድኖችን፣ ማህበራዊ ድርጅቶችን እና ሌሎች ለትርፍ የማይሰሩ ቡድኖችን ያጠቃልላሉ።

| ተጨማሪ ጥልቅ መረጃ ለማግኘት ስዕሉ ላይ ወይም ማስፈንጠሪያዎቹን ይጫኑ | |
|---|---|
| **የሥራ ቅጥር ሁኔታዎ ምንድን ነው?**<br><br> | ስራ የመቀጠር መብቶችዎ የስራ ቅጥር ሁኔታዎ ላይ የተመሰረቱ ናቸው።<br><br>ቀጣሪዎ መደበኛ ስራ የሚሰጥዎ፣ ስራው መቼና የት መሰራት እንዳለበት የሚነግርዎ ከሆነ እርስዎ **ሰራተኛ** ነዎት። **የቀን ሰራተኛ** በቀጣሪው መደበኛ ወይም የተረጋገጠ የስራ ሰዓቶች የማይሰጠው ሲሆን የዚህ ምሳሌ ተራ ሰራተኞች ወይም የወቅት ሰራተኞች ናቸው።<br><br>በሁለቱም ሁኔታዎች ቀጣሪዎ እርስዎን ወክሎ ግብር እና ብሔራዊ የመድን ዋስትና የሚከፍል ሲሆን እርስዎ እንደ ከክፍያ ጋር የሚሰጥ የዓመት እረፍትና ዝቅተኛ የላብ ዋጋ ክፍያ የመሳሰሉ መሰረታዊ የቅጥር መብቶችን የማግኘት መብት አሉዎ። የትርፍ ሰዓት ስራ የሚሰሩ ከሆነ ልክ እንደ ሙሉ ሰዓት ሰራተኞች ሁሉ ተመሳሳይ መብቶች አሉዎት።<br><br>ተጨማሪ መረጃ ከ ክፍል ሠ( E) – የስራ ቦታ መብቶችዎ ላይ ማግኘት ይችላሉ። |
| **መልማይና ቀጣሪ ድርጅቶች**<br> | መልማይ ድርጅቶች ክፍት የሥራ መደቦችን ለመሙላት ቀጣሪዎችን ወክለው ተስማሚ እጩዎችን ለመፈለግ ይሰራሉ። መልማይ ድርጅት እርስዎን **በፍጹም** ስራ በማግኘትዎ ክፍያ ማስከፈል የለበትም።<br><br>አንዳንድ መልማይ ድርጅቶች ለሌሎች የንግድ ድርጅቶች ሰራተኞች ፈልገው ሊያገኙ ይችላሉ ሆኖም የሰራተኞች ክፍያን በራሳቸው ይከፍላሉ። እነዚህ ቀጣሪ ድርጅቶች ይባላሉ። በዚህ ጊዜ እርስዎ የኤጀንሲ ሰራተኛ ይሆናሉ። ይህ በአብዛኛው የሚሰራው ለአምራችና የመጋዘን ዘርፎች ነው። |
| **የቅጥር ውሎች**<br><br> | የሥራ ግብዣ ሲቀርብልዎ፣ ቀጣሪዎ ለእርስዎ በአብዛኛው የሥራ ቅጥር ውል ተብሎ የሚጠራውን 'የስራ ቅጥር ዝርዝሮች የጽሁፍ መግለጫ' መስጠት አለበት። ይህ የእርስዎን መብቶች እና ግዴታዎች የሚገልጽ ህጋዊ ስምምነት ነው። ለኤጀንሲ ሰራተኞችም ከመጀመሪያው የሥራ ቀን ጀምሮ የስራ ቅጥር ዝርዝሮች የጽሁፍ መግለጫና መሰረታዊ የስራ ቅጥር መብቶች መስጠት አለባቸው።<br><br>ቋሚ ውሎች በግልጽ የሚቀመጥ የሥራ ቅጥር ማብቂያ ቀን የላቸውም። የተወሰነ ጊዜ ወይም ጊዜያዊ ውሎች በግልጽ የሚቀመጥ የሥራ ቅጥር ማብቂያ ቀን አላቸው። የ 'ዜሮ ሰዓት ውል' ምንም በግልጽ የተቀመጡ ዝቅተኛ የስራ ሰዓቶች የሌሉበት ስምምነትን ይገልጻል። |
| **ልምምዶች** | ልምምድ ሰራተኛው የተወሰነውን የስራ ጊዜውን በአገር አቀፍ ደረጃ እውቅና ወደተሰጠው የብቃት ደረጃ የሚወስድ ስልጠና ላይ የሚያሳልፍበት ክፍያ የሚከፈልበት የስራ ቅጥር አይነት ነው።<br><br>ብዙ ሰዎች ልምምዶች የሚያስፈልጉት ለወጣቶች ብቻ ነው ብለው ያምናሉ፣ ነገር ግን በየትኛውም የዕድሜ ደረጃ ላይ የሚገኝ ሰው ልክ እንደማንኛውም ሌላ ስራ ሁሉ ለልምምድ ሊያመለክት ይችላል። ሆኖም የተለማማጁ ዝቅተኛ የላብ ዋጋ ክፍያ ከሌሎች ስራዎች በእጅጉ ያነሰ ነው።<br><br>የልምምድ ስልጠና በመንግስት የገንዘብ ድጋፍ የሚደገፍ በመሆኑ አንዳንድ የስደተኞች ቡድኖች ይህን አይነቱን ስራ ማግኘት ላይችሉ ይችላሉ።<br><br>ስለ ልምምዶች የተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ከመንግስት ድረገጽ ላይ ማግኘት እና በቅርብዎ የሚገኙ |

| | |
|---|---|
| | የልምምድ እድሎችን አውጥተው ማየት ይችላሉ። |
| **የራስ ስራ መስራት**   | **የራሳቸውን ስራ የሚሰሩ** ሰዎች የራሳቸው ኩባንያ ወይም የንግድ ድርጅት ያላቸው ሲሆኑ እንዴትና መቼ እንደሚሰሩ ኃላፊነት ይወስዳሉ። እነዚህ ሰዎች የራሳቸውን ግብር እና ብሔራዊ የመድን ዋስትና ይከፍላሉ። እነዚህ ሰዎች ከሰራተኞች ወይም የቀን ሰራተኞች ጋር ተመሳሳይ የስራ ቅጥር መብቶችና ኃላፊነቶች የላቸውም። እርስዎ የራስዎን ስራ የሚሰሩ ከሆነና በዓመት ከ £1000 በላይ ገቢ የሚያገኙ ከሆነ ለግብር ዓላማዎች በ HMRC መመዝገብ አለብዎት።<br><br>እርስዎ የአንድ ኩባንያ የቀን ሰራተኛ/ሰራተኛ ሊሆኑ ይችላሉ፣ ነገር ግን በተመሳሳይ ጊዜ የራስዎ የንግድ ድርጅት ሊኖርዎና የራስዎን ስራ ሊሰሩ ይችላሉ። |

## ዋና ዋና ነጥቦች

1. **ኤጀንሲዎችን ጨምሮ ሁሉም ቀጣሪዎች ለእርስዎ ስለ ስራዎ ድንጋጌዎችና ሁኔታዎች የተመለከተ የጽሁፍ መግለጫ የመስጠት የህግ ኃላፊነት አለባቸው።**
2. **እርስዎ የቀን ሰራተኛ ወይም ሰራተኛ ከሆኑ መሰረታዊ የስራ ቅጥር መብቶችን የማግኘት መብት አሉዎ። ይህ የኤጀንሲ ሰራተኛ ቢሆኑ ወይም የትርፍ ሰዓት፣ ተራ ወይም የዜሮ ሰዓት ውል ሰራተኛ ቢሆኑም ጭምር ተፈጻሚ ይሆናል።**

# ጠቃሚ ማስፈንጠሪያዎችና የመረጃ ምንጮች

- መንግስት የተቀጣሪ ሰዎችና የስራ መደቦች ብዛትን የተመለከተ መረጃ የሚይዝ ወርሀዊ ስታቲስቲክስ ያወጣል።
- ይህ *መመሪያ* ዩኬ ውስጥ በመንግስትና የግሉ ዘርፍ መካከል ያሉ ልዩነቶችን እና ለእያንዳንዱ ዘርፍ የመስራት ጥቅሞች/ጉዳቶችን የተመለከተ ጠቅላላ መረጃ ይሰጣል።
- የቻርተርድ የሰራተኞችና ልማት ተቋም በቅጥር ውል ውስጥ ምን መካተት እንዳለበት የተመለከተ ተጨማሪ መረጃ አለው።
- መረጃ ስለቀጣሪ ኤጀንሲዎችን የተመለከቱ ህጎች
- ይህ በዝቅተኛ ገቢ የግብር ማሻሻያ ስር የራስን ስራ ለመስራት ጠቃሚ መመሪያ ሲሆን በተጨማሪም ሰራተኛ ወይም የራስዎን ስራ የሚሰሩ ስለመሆንዎ ለይተው እንዲያውቁ የሚረዳዎትን መረጃ ይይዛል።

# በዩኬ ውስጥ የመስራት ቱል ኪት

## ስራ መፈለግና ማመልከት

አብዛኞቹ ክፍት የስራ ማስታወቂያዎች የሚገኙት በኦንላይን ነው። ይህ ማለት ኮምፒውተር እንዴት እንደሚጠቀሙ ማወቅ ይጠበቅብዎታል ማለት ነው። ሆኖም አሁንም ማንኛውም ክፍት የስራ መደቦች እንዳሏቸው ለመጠየቅ የአካባቢ ቀጣሪዎችን ደጅ መጥናትም ጠቃሚ ሊሆን ይችላል።

ለስራ መደቦች እንዴት ማመልከት እንደሚቻል የተመለከቱ ብዙ መረጃዎችና ምክሮች አሉ። ይህ ክፍል መሰረታዊ ነገሮችን ይዳስሳል።

በዚህ ክፍል መጨረሻ ላይ ስለ ሲቪዎችና ሽፕ ደብዳቤ አጻጻፍ ጥሩ ምክር የሚሰጡዎ ድረገጾችን ዝርዝር ያገኛሉ።

**ተጨማሪ ጥልቅ መረጃ ለማግኘት ስዕሉ ላይ ወይም ማስፈንጠሪያዎቹን ይጫኑ**

| | |
|---|---|
| **የስራ ፍለጋ ድረገጾች**<br> | የሚተዋወቁ ክፍት የስራ መደቦችን ሊያገኙባቸው የሚችሏቸው በመቶዎች የሚቆጠሩ የተለያዩ የስራ ድረገጾች ወይም የሥራ ቅጥር ድረገጾች አሉ። ከእነዚህ መካከል በጣም በአብዛኛው ጥቅም ላይ የሚውሉትን ከአንዳንድ እንዴት ለእርስዎ ተስማሚውን እንደሚመርጡ ከተመለከቱ ምክሮች ጋር [እዚህ ላይ](#) ማግኘት ይችላሉ። የቅጥር ኤጀንሲዎች ብዙ ጊዜ የሥራ ቅጥር ድረገጾችን ይጠቀማሉ።<br><br>በተወሰኑ ሙያዎች ወይም የስራ ዘርፎች ላይ የተካኑ አንዳንድ ድረገጾች አሉ። [የበጎ አድራጎት ሥራ](#) በሶስተኛው ዘርፍ በሰፋት ጥቅም ላይ ከሚውሉት መካከል አንዱ ምሳሌ ነው።<br><br>ብዙ ኩባንያዎች በድረገጻቸው ላይ ክፍት የስራ መደቦችን የሚዘረዝሩ ገጾች ያሏቸው ሲሆን በራሳቸው ገጽ ላይ በቀጥታ ሊያመለክቱ ይችላሉ። ይህ ለትላለው የንግድ ድርጅቶች የበለጠ የተለመደ በመሆኑ በእርስዎ ኢንዱስትሪ ውስጥ የሚሰሩ ዋና ዋና ኩባንያዎችን የሚያውቁ ከሆነ ወቅታዊ መረጃዎችን ለማግኘት በእነዚህ ገጾች ላይ መመዝገብ አለብዎት። |
| **የትስስር መረብ**<br> | የትስስር መረብ ጠቃሚ ዘዴ ሲሆን ብዙ ሰዎች ስራዎችን በጓደኞች፣ ቤተሰቦችና የቀድሞ የስራ ባልደረቦቻቸው በኩል ያገኛሉ። ይህ ዩኬ ውስጥ እነዚህ የትስስር መረቦች ከሌሉዎት የበለጠ ከባ ቢሆንም [እነዚህን የሚፈጥሩባቸው መንገዶች](#) አሉ።<br><br>ለትናንሽና መካከለኛ የንግድ ድርጅቶች ክፍት የስራ መደቦች ካሏቸው ለመጠየቅ ሲቪ እና ሽፕ ደብዳቤ መላክ ጠቃሚ ነው። እነዚህ ኩባንያዎች ሁልጊዜም የተመደቡ የኤችአር ሰራተኞች ላይኖሯቸው የሚችል በመሆኑ የስራ መደቦች ሁልጊዜም ላይተዋወቁ ይችላሉ። ኩባንያዎቹ አሁን ላይ ምንም ክፍት የስራ መደቦች ባይኖሯቸውም እንኳ ይህን ማድረግ እንደ ውይይት መጀመሪያ ዘዴ ስለሚያገለግል ኩባንያዎቹ ወደፊት አዲስ ነገር ሲኖር ያስታውሱዎታል።<br><br>[LinkedIn](#) ለስራ ለሚፈልጉ ባለሙያዎች በጣም የታወቀ የኦንላይን ኔትዎርኪንግ ድረገጽ ነው።[እዚህ ላይ](#) ስራ በሚፈልጉበት ወቅት የትስስር ገጹን እንዴት ለእርስዎ በሚጠቅም መልኩ መጠቀም እንደሚችሉ የተመለከቱ አንዳንድ ጠቃሚ ምክሮች ተገልጸዋል። |
| **ሊተላለፉ የሚችሉ ክህሎቶች**<br> | [ሊተላለፉ የሚችሉ ክህሎቶች](#) ለሁሉም ስራ ሊጠቀሟቸው የሚችሏቸው ክህሎቶች ናቸው። አንዳንዶቹ በስራ ማመልከቻ ላይ ለመግለጽ ቀላል ናቸው፤ ለምሳሌ፡ የፕሮጀክት አስተዳደር እና የአይቲ IT ክህሎቶች። ሌሎች ሊተላለፉ የሚችሉ ክህሎቶች ግንኙነትን መመስረትን እና ለዝርዝሮች ትኩረት መስጠትን ያጠቃልላሉ።<br><br>ሊተላለፉ የሚችሉ ክህሎቶች ዩኬ ውስጥ እጅግ አስፈላጊ ተደርገው ይወሰዳሉ። ቀጣሪዎች ሊተላለፉ የሚችሉ ክህሎቶች ያሉትን ሰው በስራ ቦታ ላይ የሚፈጠሩ ለውጦችን ለመቀበል ዝግጁ እንደሆነ አድርገው ይወስዳሉ። ብዙ የስራ ዝርዝሮች ኩባንያው የሚፈልጋቸውን የተለያዩ ክህሎቶች ይዘረዝራሉ። ሁሉም የሚጠየቁት ክህሎቶች ላይኖሩዎት ይችላሉ፣ ነገር ግን ሊተላለፉ የሚችሉ ክህሎቶችዎ ከእነዚህ ጋር በጣም ተመሳሳይ ሊሆኑ ይችላሉ። |
| **ሲቪ እና ሽፕ ደብዳቤ**<br> | ሲቪ ወይም የትምህርትና ስራ ማስረጃ የትምህርት ደረጃዎን፣ ክህሎቶችዎን፣ የስራ ልምድዎንና የቅጥር ታሪክዎን የሚገልጽ ሰነድ ነው። ትክክል ወይም ስህተት የሚባል የሲቪ አጻጻፍ ዘዴ የሌለ ቢሆንም ጥቂት መከተል ያሉብዎ መሰረታዊ ህጎች አሉ።<br><br>• ግልጽ መዋቅር ይጠቀሙ |

| | |
|---|---|
| | • ጽሁፍዎን አጭር ያድርጉ<br>• ስህተቶችን ያስወግዱ<br>• ጽሁፍዎን ከስራ ድርሻዎ ጋር ያገናኙ<br><br>በሲቪዎ ውስጥ መካተት የሌለባቸው ነገሮች<br><br>• አግባብይ/ሙያዊ ያልሆነ የኢሜይል አድራሻ<br>• ፎቶግራፍ<br>• የግል ዝርዝሮች |
| **የማመልከቻ ቅጾች**<br> | ቀጣሪዎች ሁልጊዜም ሲቪ አይጠይቁም። አንዳንድ ጊዜ የማመልከቻ ቅጽ እንዲሞሉ የሚጠይቁዎ ሲሆን ቅጹ በአብዛኛው በኦንላይን የሚሞላ ነው። እዚህ ላይ አብዛኞቹን መረጃዎች ቆርጠው የሚለጥፉ እንደመሆኑ ሲቪዎ ይጠቅምዎታል።<br><br>[የስራ ማመልከቻ](#) በሚሞሉበት ወቅት ሁልጊዜም ስለ ማመልከቻዎ ተጨማሪ ማብራሪያ እንዲሰጡ የሚጠይቅዎ ክፍል አለ። ይህ ከሽፋ ደብዳቤ ይልቅ ተጨማሪ ዝርዝር ይፈልጋል።<br><br>ክፍት የስራ መደቦች አብዛኛውን ጊዜ ስራው ምንን እንደሚይዝ፣ እና ስራውን ለመስራት የሚያስፈልጉ ክህሎቶች፣ እውቀትና ልምድን ከሚዘረዝሩ የስራ ዝርዝርና ተፈላጊ ችሎታ ጋር ይተዋወቃሉ።<br><br>ይህን ክፍል በሚሞሉበት ወቅት መልስዎን በተቻለ መጠን ምሳሌዎች እየሰጡ ከዚህ ዝርዝር ጋር ማዛመድ አለብዎ።<br><br>አብዛኛውን ጊዜ ለስራ ማመልከቻ ማብቂያ ቀነ ገደብ አለ። ይሁንና እስከ መጨረሻው ደቂቃ ድረስ አይጠብቁ! |
| **ቃለ መጠይቅ**<br> | [የሥራ ቃለ መጠይቅ](#) ገጽ ለገጽ፣ በስልክ ወይም በቪዲዮ ኮንፍረንስ ሶፍትዌር አማካኝነት ሊካሄድ ይችላል።<br><br>ለቃለ መጠይቅ አስቀድመው መዘጋጀት ያለብዎ ከመሆኑም በተጨማሪ ስለ ኩባንያውና የስራው የሥራ ድርሻ የሚችሉትን ያክል ማጥናት አለብዎ።<br><br>ለእነዚህ የእርስዎን መልሶች መለማመድ እንዲችሉ ቀጣሪዎች ሊጠይቋቸው የሚችሏቸው አንዳንድ የተለመዱ ጥያቄዎች አሉ። ምሳሌዎቹ የሚከተሉትን ያጠቃልላሉ፡<br><br>• ስለ ራስዎ ሊነግሩን ይችላሉ?<br>• እዚህ መስራት ለምን ፈለጉ?<br>• ጠንካራና ደካማ ጎኖችዎ ምንድን ናቸው?<br>• ስራዎን እንዴት ያከናውናሉ?<br>• አስቸጋሪ ሁኔታን ለመፍታት ጥረት ስላደረጉበት ጊዜ ምሳሌ ሊሰጡኝ ይችላሉ?<br><br>በቃለ መጠይቁ ማብቂያ ላይ ማንኛውም ጥያቄዎች ካሉዎ ተብለው ሊጠየቁ ይችላሉ። ጥያቄዎችዎ ተገቢ መሆናቸውን ያረጋግጡ። ስለ ስልጠና ዕድሎች ወይም የእለት ከእለት የስራ ባህል በተመለከተ ሊጠይቁ ይችላሉ። |
| **ዋቢዎች**<br> | [ዋቢዎች](#) ስለ እርስዎ የስራ ልምድ፣ ክህሎቶችና ባህሪ ሊናገሩ የሚችሉ ሰዎች ናቸው። አብዛኞቹ ቀጣሪዎች ሁለት ድጋፍ ሰጪዎችን የሚጠይቁ ሲሆን ከእነዚህ አንዱ በጣም የቅርብ ስራ አስኪያጅዎ መሆን አለበት። ስራ አስኪያጅ ስለ እርስዎ ሊተላለፉ የሚችሉ ክህሎቶች ሊናገር ይችላል፤ ለምሳሌ፡ በስራዎ ላይ የተደራጁና ጥሩ ችግር ፈቺ እንደሆኑ።<br><br>ለአንዳንድ ለዩኬ አዲስ ለሆኑ ሰዎች ይህን መረጃ ማቅረብ አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል። ሁሉም የስራ ድጋፍ ሰጪዎችዎ ውጭ አገር የሚገኙ ከሆነ እንግሊዘኛ ሳይቸገር መናገር የሚችለውን ድጋፍ ሰጪ ሊያካትቱ ይችላሉ።<br><br>የባህሪ ድጋፍ ሰጪዎች ማንኛውም ስለ ጥሩ የግል ስብእናዎችዎ ሊናገር የሚችል ሰው ሊሆኑ የሚችሉ ሲሆን የበጎ ፍቃደኝነት ስራ ታማኝነትዎን፣ ሀቀኝነትዎንና መልካም ባህሪዎን መናገር የሚችሉ ድጋፍ ሰጪዎች ለማግኘት ተመራጭ ዘዴ ነው። |

| | |
|---|---|
| ዋና ዋና ነጥቦች | 1. **የስራ ፍለጋዎን በጣም ተገቢ በሆኑ ድረገጾች ላይ ያድርጉ።**<br>2. **ሲቪዎ አጭር መሆን ያለበት ሆኖ ምንም የፊደል አጻጻፍ ስህተት አለመስራትዎን ያረጋግጡ።**<br>3. **ሊተላለፉ የሚችሉ ክህሎቶች ዩኬ ውስጥ በጣም አስፈላጊ ናቸው። ስለ የግል ጥንካሬዎችዎ እና ድክመቶችዎ ያስቡ።** |

# ጠቃሚ ማስፈንጠሪያዎችና የመረጃ ምንጮች

ዩኬ ውስጥ ለስራ እንዴት እንደሚያመለክቱ የተመለከቱ በመቶዎች የሚቆጠሩ መመሪያዎች አሉ። ጥቂት እጅግ ጥሩ ምሳሌዎች እዚህ ላይ ተገልጸዋል፥

- ወደ ስራ መመለስ ቱል ኪት
- የስራ አመልካች ቱል ኪት
- ሸኘ ደብዳቤ እንዴት እንደሚጻፍ
- ጥቂት የሸኘ ደብዳቤ ምሳሌዎች
- ጥቂት ሊተላለፉ የምችሉ ክህሎቶች ጥቅሞች
- 20 የጥሩ ቃለ መጠይቅ ፍንጮች
- የስደተኛ ስራ ቅጥር ትስስር መረብ (The Refugee Employment Network) ለስደተኞች በመላው ዩኬ ውስጥ ጥሩ የስራ እድሎችን መፍጠር ላይ የሚያተኩር ብሔራዊ የአባልነት ትስስር መረብ ነው። በድረገጹ ላይ በመደበኛነት የሚሻሻሉ የስራ እድሎች ይገኛሉ።